ፓኖራማ ቁጥር 57

የትዝብት አድማስ

ታህሣሥ 24 2001 ዓም

<u>ሳቅ፥ ዓለም አብሮህ ይስቃል፥ አልቅስ፥ ብቻህን ታለቅሳለህ</u>

ታላላቅ የሃይማኖት መጻሕፍት ፥ከሚስቀው ጋር ደስ ይበልህ፥ ከሚያለቅሰው ጋር ደግሞ የሀዘን ተካፋይ ሁን የሚል ትምሕርት ቢያስተምሩም፥የምንኖርባት ዓለም ግን ምናልባት ከተደሰተው ጋር አብራ ትጨፍር እንደሁ እንጅ፥ ከሚያለቅሰው ጋር ግን አብራ ለማልቅስ እምባ ያላት አትመስልም፡፡ ለከፋው እንባዋን ልትለግስ ቀርቶ፥ እንዲያውም " እፊቴ ላይ አታልቅስብኝ" ብላ የምታባርረው ነው የምትመስል፡፡ በዛሬው ዘመን፥ የኢትዮጵያ ሕዝብ በወያኔ የዘረኞች አገዛዝ ስር ወድቆ የደም እምባ ሲያለቅስ እያዩ፥ ዓለምና ጊዜ ተባብረው፥

" ወያኔ አይከሰስ ቀማኛና ዳኛ፥
ዕድልክን አማርር ምን እናድርግ እኛ" ብለው ደምድመዋል፡፡

እነርሱ እቅጩን ቢነግሩንም፥ብዙዎቻችን ግን አሁንም ተስፋ ሳንቆርጥ፥ ለሀገራችን መፍተሄ የሚሆንልን መድሃኔት ከውጭ ይመጣልናል ብልን በጉጉት እንጠብቃለን፡፡ ይህ እንደማይሆን ግን ስንቶቻችን እንደተገነዘብነው ማወቅ ያስቸግራል፡፡እስከ ፍጻሜ-ዓለም በተስፋ ብንጠብቅ፥ዓለምና ጊዜ የራሳቸውን ፍሰሀና ሀሴት ከማሳደድ በቀር፥የእኛን የመከራ ዕምባ ያደርቁልናል ማለት አንችልም፡፡ የሚያስቅ ነገር በአጋጣሚ ካጋጠምንና አብሮን የሚስቅ ከመጣ ፥በትዝብት እያየን ከመገርም በስተቀር፥ስንስቅ አብሮን የሳቀው ሁሉ ግን፥የለቅሷችንም ተካፋይ ይሆናል ብለን ማመን ቀርቶ ማሰብም የለብንም፡፡

ኢትዮጵያ፥ ሳቋን አይቶ የሚስቅላት፥ለቅሶዋን ሰምቶ የሚያዝንላት ወዳጅ ለማትረፍ ከፈለገች ፥ከሁሉ በፊት፥እርሷ እራሷ፥የሳቋ አዘጋጅ፥ የለቅሶዋ አስወጋጅ ሆና መገኘት ይኖርባታል፡፡ ይህንን ክስተት ልታመጣ የምትችለው ደግሞ፥ ዜጎቿ በሁለንተናዊ ረገድ፥ የራሳቸውና የሀገራቸው ዕድል ወሳኞች ሆነው ሲገኙ ብቻ፡፡ ይህንን ሀቅ በተመለከተ፥ በአሁኑወቅት የኢትዮጵያ ዜጎች በማነኛውም አቅጣጫ ቢያማትሩ የራሳቸውን ዕድል ለመወሰን ቀርቶ፥እነርሱም እንደ ሕዝብ ኢትዮጵያም እንደ ሀገር ለመቆየት የሚያስችላቸውን ሁኔታ እንኳን ለማየት ከቻሉ፥ዕድለኞች ናቸው፡፡ስለ እራስ መቻል በተመለከተ፥መባል

የሚቻለው ሁሉ ስለተባለ፥ስለዚህ ሀቅ ብዙ ማለት ጊዜ ማጥፋትና አሰልች

መሆኑን ብንገነዘብም፥ጉዳዩ፥እራሳችንን ችለን ማንነታችንን ለዓለም እስከ ምናሳውቅበት ወቅት እየተንከባለለ ከኛው አልፎ ተርፎ፥ ወደትውልድ እንደሚተላለፍ ልንረሳው አንችልም፡፡ መሳቅና ማልቀስ፥ መጠቃትና ማጥቃት ፥ማግኘትና ማጣት፥በህይወት ሂደት ውስጥ ተፈራራቂ በመሆናቸው፥ የአሁኑ የሀገራችን ሁኔታ ተወደደም ተጠላ፥ፈጠነም ዘገየ፥ መለወጥ እንዳለበት ብቻ ሳይሆን፥ በግድ የሚለወጥ መሆኑንም የኢትዮጵያ ሕዝብ ከልብ ያምንበታል፡፡ ወያኔን ተቃውሞ የሞት-ሽረት ትግል የሚያደርገውም ከዚህ ፅኑ ዕምነት ከመነጨ ተስፋና ራዕይ ነው፡፡ተስፋውንና ራዕዩን ስኬታማ ለማድረግ የተነሳን ሕዝብና ቀፎው የተቀሰቀሰበትን ንብ ሊያቆመው የሚችል ምድራዊ ኃይል እንደሌለ የየካቲት ሕዝባዊ አመፅ የቅርብ ትዝታ መሆኑ ብቻ ሳይሆን፥የዓለም ዐብዮት ታሪክም ያረጋገጠው ሀቅ ነው፡፡ ዳግማዊ የካቲት እንዳይመጣ መለስና ጓደኞቹ የተቻላቸውን ያህል ለመከላከል ቢጥሩም፥ከመምጣት እንደማያስቀሩት ግን በሚመገባ ያውቁታል፡፡ ያም ሆኖ በአሁኑ ወቅትአሃዙ በትክክል ለማወቅ ያለተቻለ ዜጋ ወኅኒ ቤት በየቀኑ እንዲወረወር ከማድረግ አልተቆጠቡም፡፡ የዓለም ልዩ ልዩ ተቋማትም ይሁን ሀገሮች ስለ ኢትዮጵያና ስለሀገራችን ሕዝብ ሰቆቃ ይስሙም አይስሙ፥ይረዱም አይረዱ፥ የየራሳቸው የሆኑ በተለያዩ ችግሮቻቸው ስለተወጠሩ፥የእኛን ለቅሶ ተረድተው እንደ ራሳቸው አጀንዳ በመውሰድ ኢትዮጵያን ይረዳሉ ተብሎ አይጠበቅም፡፡

የዛሪይቱ ዓለም፥በኢኮኖሚ ድቀት፥በሥራ ዕጦት፥ በጦርነት ውድመት፥ በአሸባሪዎች ጥቃት፥ በሰብዓዊ መብቶች መጣስ፥ በአየር ብክለት፥ወዘተ ተወጥራ ተይዛ መግቢያ ቀዳዳ ባጣችበት ወቅት፥ ስለኢትዮጵያ መከራና ስቃይ ትኩረት ትሰጣለች ብሎ ተስፋ ማድረግ፥የሁኔታዎችን ውስብስብነት አለመረዳት ብቻ ሳይሆን፥ የዓለምን ሁኔታና ትኩረት በሚገባ አልመገንዘብ ነው፡፡ሁለት ሰዎች አብረው ሲሄዱ ዐይኖቻቸው ውስጥ በርበሬ ቢገባ ሁሉም የየራሱን ዓይን ከመቃጠል ለማዳን ይፍጨረጨራል እንጅ፥ አንዱ የራሱን ዓይን ቃጠሎ ሳያድን ለሌው ዓይን ያስባል ማለት ሞኝነት ብቻ ሳይሆን፥ የማይጠበቀውን መጠበቅ ይሆናል፡፡ ዛሬ መላው ዓለም፥ የራሱን የተወሳሰበና የተደራረበ ችግር መቋቋም አቅቶት እርስ በዕርሱ በሚፋተግበት አስቸጋሪ ወቅት፥ ስለ ኢትዮጵያ ችግር ደንታ ሊያሳይ ይችላል ተብሎ የሚጠበቅ እንዳልሆነ መታወቅ ይኖርበታል፡፡ ዓለም ልትስቅልን የምትችለው እኛ መሳቅ ስንችል መሆኑን ብንረዳም ቅሉ፥ እኛ ዛሬ እንኳን የምንስቀው የምንገጥጠው የለንም፡፡ ለነገሩማ ከመግጠጥ መሳቅ በብዙ መልኩ ይሻል ነበር፡፡ "ሳርር እስቃለሁ እንደማሽላ፥ ነገር በሆዴ እየተብላላ" እየልን የአስመሳይ ህይወት መምራት የምንችል ሕዝቦች መሆንን አንፈልግም፡፡ ይህን ባኅርይ ለፀሀፍ-ፈርሳውያን እንተውላቸዋለን፡፡

ይህንን ርዕስ የመረጥነው፥ስለ ሀገራችን ዘርፈ ብዙ ቸግሮችና ስለ ሕዝቡም ሰቆቃና ውርደት ለመዝርዝር አይደለም፡፡ይህ ጉዳይ ለአለፉት አስራ ስምንት የመከራ ዓመታት በልዩ ልዩ መንገዶች ተዘርዝሮ ተዘርዝሮ፥ እንኳንስ መላውን ዓለም ቀርቶ፥ እኛኑን በለጉዳዮችን
ሳይቀር ያሰለቸና ያስመረረ ጩኸት ከሆነ ቆይቷል፡፡በዚህ ሳምንት የገባውን

*የፈረጆቹን አዲስ ዓመት ምዕራባውያን ሲያከብሩ÷ሲስቁ ሲደሰቱ÷ እኛም የዓለም ኅብረተሰብ አባሎች እንደመሆናችን÷ መልካም አዲስ ዓመት ይሆንላችሁ ማለቱ የመልካሙ ባኀላችን ነፀብራቅ እንደሆነ ይገባናል፡፡ ምናልባትም÷የደስታቸው ተካፋዮች ለመሆን በምንጣጣርበት ወቅት÷ ትህትና የተጎናፀፈ ፈገግታም ማሳየቱ÷ አብሮ ለመኖር ብቻ ሲባል የሚደረግ የዲፕሎማቲክ አገላለጽ እንደሚሆን በሀገራቸው ጉዳይ ልባቸው የሚደማው የኢሕአፓ ታጋዮች ይገነዘቡታል፡፡ ከግንዛቢያቸው በስተጀርባ ያለውን ተጨባጩን የሕዝባቸውን ጭቆና ተጋርተው በማንገብ የሚያደርጉትን ፍልሚያ ግን ዓለም እንዲስቅልን እኛም እንሳቅ በማለት÷ አስመሳይ ሳቅ በመሳቅ እራሳቸውን አያታልሉም፡፡ የትግል ትኩረታቸውና ዓይነተኛ ዒላማቸው÷የሀገራቸውን ስትራተጂያዊ ጠላት ወያኔን አስወግዶ ሕዝባቸውን ከዘረኞች አገዛዝ ነፃ ማውጣት ነው፡፡ ይህ ደግሞ÷ የደስታቸውና የርካታቸው ሶአልፋና ኦሚጋነው፡፡*

*ምዕራባውያኑ አዲሱን ዓመት የሚቀበሉት÷ ለሕዝባቸው መልካሙን በመመኘ ት÷ የኢኮኖሚዕድገቱን በማሳደግ÷ የነፃነትና የዲሞክራሲ መብቱን በማረጋገጥ ÷አዳዲስ የዕድገት ዕቅዶች በመትለም ሲሆን÷ በዘረኞቹ አገዛዝ የምትማቅቀው ሀገራችን ግን ዛሬ÷ ዜጎቿ በገፍ ወኅኒ የሚወረወሩባት÷ በጭካኔ የሚገደሉባት÷ ምሁራን የሚሰደዱባት÷የተቃዋሚ ፖለቲካ ድርጅት መሪዎች እንበለ-ፍርድ የሚታሰሩባት÷ረሃብ ቸነፈር÷ ዋይታና ለቅሶ የሚሰማባትናየሰፈነባት÷ሰለምና መረጋጋት የጠፋባት የምድር ሲዖል ሆናለች፡፡ ዓለም እንዲስቅላት ለመሞከር በምታደርገው ጥረት መሳቂ ቀርቶ÷ ዓለም አንጀቱ እራርቶላት እንዲያዝንላት ብላ ለማልቀስ እንኳን አምባዋ ደርቋል፡፡ለመሳቅ ከልብ የመነጨና ከውስጥ የፈለቀ ደስታ እንደሚያስፈልግ ሁሉ÷ ለማልቀስም እንኳ እምባ ያስፈልጋል፡፡“ ከልብ ካዘኑ አምባ አይገድም” የሚለውን ይትብሃል ብንረዳም ቅሉ÷ የሀገራችን እምባ ከደረቀ ቆይቷል፡፡የዕምባው መድረቅ ምክንያት የሳቁ ምንጭ÷የዕምባውን ቦታ ስለወሰደው ሳይሆን÷ዜጎቿ÷አልቅሰው አልቅሰው እምባቸው ስለነጠፈባቸ ው ነው፡፡ ኢትዮጵያ ዛሬ ዓለም እንዲስቅላት በመፈለግ የሌላትን ሳቅ ለመሳቅም ይሁን÷*

*እንዲያዝነላትም ብላ ለማለቀስ እምባዋ ደርቋባታል፡፡ የሀገራችንን የመከራ እምባ በማድረቅ ዘለዓለማዊና የማያቋርጥ ሳቅ እየሳቀች በደስታና በብልፅግና ተከብራ እንድትኖር÷ ወያኔን ለማስወገድ ትግላችንን ከማፋፋም የበለጠ ሌላ ተግባር አይኖረንም፡፡ያን ጊዜ÷ዛሬ ሀገራችንንየረሳት ዓለም÷ አክብሮና አድንቆ የደስታዋ ተካፋይ እንደሚሆን አንጠራጠርም፡፡ ያ ወቅት እንዲመጣ÷ ሁሉም ዜጋ የዜግነቱን ድርሻ እንዲወጣ ይጠበቅበታል፡፡ፓርቲያችን ሲመሠረት የገባውን ብሔራዊ ቃል ኪዳን በመጠበቅ ትግሉን ከማፋፋም ወደኋላ እንደማይል ወያኔዎቹ ከማንም ያላነሰ ያውቁታል፡፡ እኛም እነርሱንና ማንነታቸውን በሚገባ እናዋቃቸዋለን፡፡ የምንጣለቸውና አምርረን የምንተገላቸው፤ የሀገራችን ስትራተጂያዊ ጠላቶች በመሆናቸው እንጅ÷ የግል ጠብና ኩርፊያ ኖሮን አይደለም፡፡ እነርሱም ሆኑ አንዳንድ ከንቱዎችና ግብዞች እንደሚሉት÷የሥልጣን ኩርፊያና የምቀኝነት አባዜ አይደለም፡፡ ሊሆንም ከቶ አይችልም፡፡ ለከንቶ ውዳሴና ለአላፊ ጠፊ÷ ለጊዚያዊ ጥቅምና*

በወረተኝነት ተወዳጅነት ለማትረፍ ተብሎ፥ በሀገራችንን ዘላቂ ጥቅም ላይ አንደራደርም፡፡ዓለም ከእኛ ጋር እንዲስቅልን ብለን የውሸት ሳቅ አንስቅም፡፡ አብሮን የሚያለቅስ ይጠፋል ከሚልም ስጋት፥ በሀገራችን ከርስ መቃብር ላይ አንሳለቅም፡፡ አንስቅም፡፡ ለሀገራችን ተንሣዔ ሙታን ስንል ግን እየሞትን እንኖራልን እንጅ፥ የውርደት ሞት እየሞትን አንኖርም፡፡ ትግላችን ህያው ሆኖ የሀገራችንን ነፃነት የሚያመጣ መሆኑን አጥብቀን ስለምናም፥ የሀገራችን ህያውነት በእኛ ኅልፍት ዘለዓለማዊ ይሆናል፡፡ “ በትግል መሞት ህይወት፥ ለሀገር- ለሕዝብ ዘለዓለማዊነት” የምንለውም፥ ከዚህ መሠረታዊ ዕምነታችንና ከአድማስ በአሻገር ከምናየው፥ብሩኅ ተስፋና ራዕይ በመነሳት ነው፡፡

ትግላችንን እንቀጥላለን!!!